በቅንጅት ስም በአለም አቀፍ ደረጃ
ተደራጅታችሁ የፖለቲካ አመራር
እየሰጣችሁ ለነበራችሁ ሁሉ
<u>በያላችሁበት</u>

ከሁሉ አስቀድመን ከእስር የተፈታነው የቅንጅት አመራሮች፣ ሌሎች አባላትና ደጋፊዎች በአጠቃላይ በእስር በነበርንበት ጊዜ እኛን ከእስር ለማስፈታት ስታደርጉ የነበረውን እልህ አስጨራሽ ትግል፣ ይህም ትግላችሁ ለመፈታታችን ያደረገው አስተዋፅኦና በእስር በነበርንበት ጊዜ የእንቅስቃሴያችሁን ሂደት በተለያዩ የሬዲዮ ጣቢያዎች በምንሰማበት ጊዜ ይሰጠን የነበረውን የመንፈስ እርካታና ብርታት በማስታወስ ለእናንተ ያለንን አክብሮትና ከልብ የመነጨ ምስጋና በመላው እስረኛ ስም ለማቅረብ እንፈልጋለን፡፡

በተለይ እኛ አመራሮቹ በታሰርንበት ወቅት፣ በአጠቃላይ የአገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በታፈነበት ሁኔታና የዴሞክራሲ ትግሉ ጭራሹኑ ይኮላሽ ይሆን ወይ? የሚል ፍርሃት በሰፊው ባንዣበበበት ጊዜ በውጭ የምትገኙ አባሎቻችን ትግሉ እንዳይሰናከል በመደራጀትና አመራር በመስጠት በተለይም በውጭ የሚገኙ ወገኖቻችንን እኛ ወደ እስር ከመግባታችን በፊት ከነበረበትም በላይ በማነሳሳትና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በማደራጀት በዲፕሎማሲው መስክ የትግላችንን ምንነት ለአለም ህዝብ እንዲታወቅ አድርጋችኋል፡፡ በዚህም በገዢው መንግስት ላይ ከፍተኛ ዲፕሎማሲያዊ ጫና እንዲያርፍበት ከማድረጋችሁም በላይ ይህ እንቅስቃሴያችሁ .ትልቅ ትርጉም ያለውና ለድርጅታችንም ሆነ ለትግሉ በቀላሉ የማይገመት ዘላቂ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡ በዚህም እጅግ የኮራንባችሁ መሆኑን እንድታውቁት እንፈልጋለን፡፡

የጀመራችሁት ስራ ሙሉ ለሙሉ እንዳልተቋጨና ለወደፊቱም ቀጣይ እንደሆነ በመገንዘብ በተለያየ መስክ በዚህ ትግል ውስጥ አገራችን እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአት እስኪሰፍንባት ድረስ ተደጋግፈን እንደምንቀጥል ምንም ጥርጥር የለንም፡፡ አበው እንደሚሉት የሰው ማንነቱ የሚታወቀው በመከራ ጊዜ ነው:: እናንተም አገራችን በገጠማት ክፉ የፈተና ጊዜ እንደደረሳችሁላት እሙን ነው፡፡ የሚሰራ ሰው ሊሳሳት ይችላል:: በሰራ ጊዜም ግጭቶች መፈጠራቸው የማይቀርና የሚያሳዝን ቢሆንም የሚገርም ግን አይደለም፡፡ ትልቁ ብልህነት ችግሮችን በመቻቻል መፍታትና ባለፈው ግጭት ከመደናቆር ይልቅ ትኩረትን በዋናው ግብ ላይ በማድረግ የወደፊቱን አላማችንን ከፍፃሜ ለማድረስ በትጋት መስራቱ ላይ ነው፡፡ እኛ ከእስር የተፈታነው የቅንጅት አመራሮች እስከ ዛሬም ስንቀሳቀስ የቆየነው ይህንን መርህ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ወደ ኋላ ካየንም የምናየው ከስህተታችን ተምረን ወደፊት የሚወስደንን መንገድ ለመጥረግ እንጂ በቀድሞ ችግሮች ለመብሰልሰል አይደለም፡፡ ይህ መንፈስ በውጭ በምትገኙ ወገኖቻችንና አባሎቻችንም ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው ከልባችን እናምናለን፡፡

ከዚህ በፊት እኛ እስር በገባንበት ጊዜና በአገር ውስጥ የነበረው ሁኔታ ምንም አላንቀሳቅስ ባለበት ወቅት፣ ቀድሞ ትሰሩት እንደነበረው በድጋፍ ሰጪ ማህበራት በመደራጀት ለድርጅታችን ድጋፍ ከመስጠት ባሻገር በተወሰነ ደረጃ የፖለቲካ አመራሩንም በመስጠት ትሰሩ እንደነበር ይታወቃል። ይህም ቅንጅቱን እጅግ ጠቅሞታል ብለን እናምናለን። በአሁኑ ጊዜ እኛ ከእስር በመፈታታችን አቋርጠነው የነበረውን የቅንጅቱን የፖለቲካ አመራር የመስጠቱን ሥራ ቀጥለናል። የድርጅታችንም ህገ ደንብ የፖለቲካ አመራር የመስጠት ሥራ በሁለት ቦታ ሊሆን እንደማይችል በግልፅ ያስቀምጣል። በመሆኑም ይህ መልዕክት ከደረሳችሁ ጊዜ ጀምሮ እኛን በመወከል ትሰጡ የነበረው የፖለቲካ አመራር መቋረጡን እያሳወቅን፣ ይህንን ሸክም ለረጅም ጊዜ ይዛችሁ በብቃት በመወጣታችሁ ለእናንተ ያለንን አክብሮትና አድናቆት እንገልፃለን። ይህንንም አዲስ የተፈጠረ ሁኔታ እናንተው እራሳችሁ ከእናንተ ጋር በትብብር ይሰሩ ለነበሩ የድጋፍ ሰጭ ድርጅቶችና ሌሎች አካላት እንድትገልፁላቸው ይሁን።

በቀጣይ ድርጅቱ በውጭ ሀገር ስለሚያደርገው አጠቃላይ እንቅስቃሴ ዓይነትና እናንተም በዚህ ስራ ስለሚኖራችሁ ድርሻ ከእናንተው ጋር በመመካከርና የድርጅቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ መሰረት በማድረግ የምንወስነው ይሆናል። ለዚሁ ሥራ ሲባል በቅርቡ ከሀገር ቤት ወደ ውጪ የሚመጣ አንድ ቡድን ይኖራል። እስከዚያው በድጋፍ ሰጪ ደረጃ እየሰራችሁት ያለውን ሥራ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ እንገልፃለን።

ኢ/ር ኃይሉ ሻውል
የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፓርቲ
ሊቀመንበር
ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ.ም